**ሳምንታዊ ዜና (የካቲት 16 ቀን 2000 ዓ. ም.)**

**ወያኔና ሻዕቢያ ውጊያ መጀመራቸው አይቀሬ ስለመሆኑ ፍንጭ ታዩ፣ ወያኔም 15 ሜትር ርዝመት ያለው ተምዘግዛጊ ሚሳኤል ወደሰሜን አጓጓዘ፣ የወያኔ ባለስልጣናት አህያዋን «የትግል አጋራችን» ብለው የኢትዮጵያን ባንዲራ አልብሰው አደባባይ አዞሯት፣ የወያኔን ምስረታ ለማክበርም በ3 ምድብ ተከፍለው ሲዝናኑ አደሩ፣ በመቀሌ ሰክረው በቡጢ ተናረቱ፣ አዲስ ወያኔ ፊጠር ፊልም ሊሰራ መሆኑ ተጋለጠ»»»»»»»»»**

**ሌላም ዜና ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ ጣቢያ** ..................

የወያኔ ባለሥልጣናት በደደቢትና እና በሽሬ እንደስላሴ እየተንደላቀቁ ሻዕቢያና ወያኔ ባካሱት ውዝግብ ምክንያት አንድ እንጀራ ቆርሶ በልቶ የማያውቀው ወታደር በድንበር በላይ ተፋጥጦ እንደሚገኝና ውጊያው በየትኛውም ሰዓት ሊጀመር እንደሚችል ከአንዳንድ የዲፕላማቲክ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ ያስረዳል፡፡

እንደ ዲፕሎማቲክ ምንጮቹ ገለፃ ከሆነ ሻዕቢያ ጦሩን ወደ ድንበር ከማስጠጋቱም በላይ ለጥበቃ የተሰማራው የሠላም አስከባሪ ኃይል ይዞት የነበረውን ቦታ ለቅቆ ሲወጣ ሻዕቢያ በምትኩ ጦሩን ማስፈሩ ገልፀው ወያኔም በኩል ጦሩን በተጠንቀቅ ላይ እንዲሆን ለጦር አዛዦች ትዕዛዝ የተሰጠ መሆኑንና የከባድ መሣሪያዎችንም ወደ ውዝግቡ ስፍራ እያስጠጉና የማስፈራሪያ መግለጫ እየሰጠ መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በተለይም የካቲት 10 ቀን 2000 ዓ.ም የወያኔ ባለሥልጣናት ደደቢት በረሀ በዓሉን ለማክበር ሽር ጉድ እያሉ በተጓዳኝ ግን ለሻዕቢያ የማስጠንቀቂያ መግለጫ አውጥተው እያስፈራሩ መሆኑ ታውቋል፡፡

የሁለቱ ቡድኖች ውጊያ መጀመር አይቀሬ በሆነበት በዚህ ወቅት የተለያዩ የጦር መኪኖች ወደ ሰሜን በኩል እየተጓጓዘ ሲሆን ወደ ምዕራብ አቅጣጫም ግዙፍ ጀኔሬተር ተጭኖ ሲጓጓዝ መመልከታቸውን የአይን ምስክሮች ለተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ገልፀዋል፡፡

በተጨማሪም የካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም ከምሽቱ 3:30 ላይ 6 ተምዘግዛጊ ሚሳኤል የጫኑ ከባድ መኪኖች 3 ቁጥር ማዞሪያ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ መታየታቸውን የአይን ምስክሮች ገለፁ፡፡



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ይኸው ከ12 - 15 ሜትር ርዝመት እንዳለው የገመቱት የአይን ምስክሮች 6 ሚሳኤል ሲሆን ከፊትና ከኋላ መትረየስ በተጠመዱ ፓትሮል መኪኖች ታጅቦ በቀለበት መንገድ ከአየር ጤና ወደ ቃሊቲ መስመር የተጓዘ ሲሆን ምናልባትም በአዋሽ አርባ አድርጐ ወደ ሰሜን ግንባር ለመጓጓዝ ሳይሆን እንዳልቀረም ግምታቸውን ሰንዝረዋል::

የቀለሙ ቅብ የአሜሪካ ወታደሮች ልብስን የመሰለው ሚሳኤል ስሪቱ የየት ሀገር እንደሆነ በትክክል ባይታወቅም የአሜሪካ ሳይሆን እንዳልቀረም ይገመታል ሲሉ ገልፀዋል::

በሻዕቢያና በወያኔ መካከል የተጀመረው የቃላት ጦርነት ወደ ጦር ማስጠጋት የተሸጋገረ ሲሆን ሰሞኑን ደግሞ ውጊያ አይቀሬ መሆኑን የሚያመላክቱ ፍንጮች እየታዩ መሆናቸውን ገልፀው ይህም ሚሳኤሉ መጓጓዙ የጦርነቱን አይቀሬነት አጠናክሮ የሚያሳይ ነው ሲሉም ጨምረው ገልፀዋል::

የሕወሓት 33ኛ ዓመት የምሥረታ በዓል ምክንያት በማድረግ በአዲስ አበባና በሌሎችም ከተሞች የትግራይ ተወላጆች መሀላ ማድረጋቸውን የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

በተለይም በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል በተደረገው በዚሁ ስብሰባ ላይ አንድ ከፍተኛ የወያኔ ባለሥልጣን የተገኘ ከመሆኑም በላይ «እስከዛሬ ድረስ ለ33 ዓመታት አንድ ላይ እጅ ለእጅ ተያይዘን እዚህ ላይ ደርሰናል:: ይሁን እንጂ ከእስከዛሬው በበለጠ በአሁን ወቅት ደግሞ አንድነታችንን አጠናክረን የሚሰነዘርብንና የታሰበብንን ጥቃቶች መመከት ይገባናል:: ይህ የሚሆነው ደግሞ ምስጢራችንን ጠብቀን ልብ ለልብ ስንናበብ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ እስከዛሬ በሀገሪቱ አሉ የተባሉ ኢንዱስትሪዎች በትግራይ ውስጥ አቋቁመናል:: አሁን ግን ከተሰራው በላይ መሥራት ይጠበቅብናል:: እናም ከመቼውም ጊዜ በላይ ለሁሉም ነገር ዝግጁ መሆን አለብን:: ስለዚህ ይህንን ደግሞ በመሀላ ልናረጋግጥ ይገባናል» በማለት ይኸው የወያኔ ባለሥልጣን መናገሩን ዘገባው አስረድቷል::

የወያኔ ባለሥልጣን በአዳራሽ የተገኙት የትግራይ ተወላጆች መሀላ እንዲፈፅሙ ባዘዘው መሠረት እጅ ለእጅ ተያይዘው እጃቸውን ከጭንቅላቻው በላይ በማውጣት መሀላ መፈፀማቸውን ይኸው ዘገባ ገልፆ ለዘመናት ተዋልዶ የኖረውን የትግራይ ሕዝብ ከሌላው ሕዝብ ጋር ለማጋጨት በማሰብ ሆን ብለው የትግራይን የበላይነት



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ለማረጋገጥ አዲስ ቅስቀሳ እየሰሩ መሆኑንም የሰበሰባው ተሳታፊዎች በቁጭት መግለፃቸውን ይኸው የደረሰን ዘገባ አስረድቷል።

በተለይ በአሁን ሰዓት በመሉ በመሉ የሀገሪቷን ሀብትና ስልጣን የተቆጣጠሩት የወያኔ ባለሥልጣናት እስከዛሬ ድረስ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ጋር የትግራይን ሕዝብ ለመነጠል ሲሰሩ የነበሩ ቢሆንም በሕዝቡ ቀራጥ እርምጃ ሳይሳካላቸው የቀረ ሲሆን አሁን ከደደቢት በተነሱ 33ኛ ዓመታቸው ላይ «ጥቃት ሊሰነዘርብን ይችላልና ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ፣ ምስጢርም ጠብቁ» እያሉ በአዲስ ሥልት የትግራይን ሕዝብ ከተቀረው ወገኑ ጋር ለማቃረን መጀመራቸው አሳፋሪና አሳዛኝ ከመሆኑም በላይ አፍራሽ ተልዕኳቸው አሁንም እንዳለ መሆኑን ያሳያል ሲሉ አንድ የትግራይ ምሁር ሲገልፁ መደመጣቸውን ዘገባው ገልጿል።

ለእነመለስና ጃሌዎቹ ቀን የወጣላቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ቁልቁል እንደካሮት የተቀበሩበት 33ኛ ዓመት የሕወሓት በዓልን አስታክከው አፍራሽ ተልእኮ የጀመሩት እነዚሁ ሰይጣናዊ አመለካከት ያላቸው ወያኔዎች የካቲት 10 ቀን 2000 ዓ.ም ደደቢት በረሀ ድረስ ወርደው ያከበሩ ሲሆን የካቲት 11 ቀን በሽሬ እንደስላሴ ከተማ በመድፍና በአየር መቃወሚያ ተከብበው ማክበራቸው ታውቋል።

እነመለስን ጨምሮ ከፍተኛ የወያኔ ባለሥልጣናት በተገኙበት በዚሁ በዓል ላይ የሽሬ እንደስላሴ ከተማ በከባድ መሣሪያዎች ተከብቦ ለአራት ቀናት የከረመ ሲሆን ይህም የሆነው የሻዕቢያ አየር ኃይል ጥቃት ሊሰነዝር ይችላል ተብሎ ስጋት ስለደረባቸው መሆኑንም ይኸው የደረሰን ዘገባ አስረድቷል።

መላው የሀገሪቷ ሕዝቦች በከፍተኛ የኑሮ ውድነት የተነሳ የእለት ጉርስ መቅመስ ተስኗቸው ባለበት በዚህ ወቅት ወያኔ 33ኛ ዓመት የምስረታ በዓል አከብራለሁ በማለት እጅግ ቁጥሩ ብዙ የሆነ ብር ከመንግስት ካዝና አውጥተው እየረጩ መሆኑ የታወቀ ሲሆን፣ ወያኔዎች የያዙት ድብቅ አጀንዳ አሁንም እንዳለና ሕዝቡን በችግርና በድህነት ለማንገላታት እንደሆነም ሁኔታውን የተከታተሉ የሀገሪቱ ዜጐች በንዴት እየገለፁ ይገኛሉ።።

ወያኔ የተወለደበት መርገምት ቀንን ለማክበር ሁሉም አባላት የበዓሉን ዝግጅት ባደረገበት ወቅት እሁድ የካቲት 10 ቀን 2000 ዓ.ም በምድብ ተከፍለው በሐገሪቷ ሕዝብ ገንዘብ ሲዝናኑበትና ሲምነሸነሹ ማደራቸውን የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ይኸው የሕወሓት ሰዎች መዝናናት በ3 ምድብ ተከፍሎ የተካሄደ መሆኑን ያጋለጡት ምንጮች ምድብ አንድ በአዲስ አበባ የወያኔውን መሪ መለስ ዜናዊን ጨምሮ የሕወሓት ፖሊት ቢሮ አባሎችን፣ ምድብ ሁለት የትግራይ ክልል ርዕሰ መስተዳድርን ጨምሮ የሕወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ በመቀሌ ምድብ ሶስት ደግሞ የትግራይ የዞን አስተዳዳሪዎችን ጨምሮ ከፍተኛ ካድሬዎች በሽሬ እንደስላሴ ሲዝናኑ እንዳደሩ ይኸው የውስጥ አዋቂ ምንጮች ዘገባ አጋልጧል።

የሐገሪቷ ሕዝቦች ቁራሽ ዳቦ ያጡት ወያኔ በዘረጋው ዘረኛና ጉጠኛ ፖሊሲ ምክንያት መሆኑ የታወቀ ሲሆን ይበልጥ ከድህነቱ በላይ ደግሞ በማንነቱ ላይ እያሾፉና እያላገጡ በገዛ ሀብቱ ሲዝናኑበት መክረማቸው አንጀት እንደሚያደብን ምንጮቹ ገልፀዋል።

እንደምንጮቹ ገለፃ ከሆነ በተለይም በዚሁ ምሽት ላይ የሕወሓት ጄኔራሎች አዲስ አበባ፣ ኮሎኔል ማዕረግ ያላቸው የሕወሓት መኮንኖች ከባለሥልጣናቱ ጋር በመቀሌ አብረው ሲዝናኑ ያመሹ ቢሆንም በተለይም በመቀሌ መኮንኖቹ እና ሲቭሎቹ ተሳክረው እርስ በእርስ በሴት ተጣልተው በቡጢ ሲናረቱ እንደነበርም አስረድተዋል።

አምና የሕወሓት 32ኛ ዓመት መቀሌ ላይ በተከበረበት ወቀት የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ፣ የትግራይ ሕዝብ እጅ ለእጅ ተያይዞ የሚመጣብንን ሁሉ መመከት አለበት በማለት ደጋግሞ ይገልፅ የነበረ መሆኑን ያስታወሰው ዘገባው ዘንድሮ በወያኔው ከፍተኛ ባለሥልጣን በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል ሰብስቦ በግዴታ መሀላ እንዲፈፅሙ ማድረጉ ያን ጊዜ የተጀመረ ሽረባ መሆኑንም ጨምሮ ገልጿል።

በጣም የሚገርመውና የሚያሳዝነው በአፍሪካውያን የነፃነት ተምሳሌት መግለጫ የሆነውን የኢትዮጵያን ባንዲራ በትግል ላይ መስዋዕትነት ከፍሏል ለተባለ አህያ አልብሰው ለሕዝቡ ማሳየታቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ መናቅና መስደብ መሆኑ በገሀድ የታየበት መሆኑም ተረጋግጧል።

ከደደቢት በረሀ ጀምረው እስከአሁን ድረስ በኢትዮጵያ ባንዲራ ላይ ያላቸው ጥላቻ እየጨመረ እንጂ ያልቀነሰላቸው ሕወሓቶች አሁን ደግሞ ብለለው ብለው አህያ ላይ ጠቅልለው ይህን የመሰለ ወራዳና አሳፋሪ ተግባር መፈፀማቸው ወትሮም ከኢትዮጵያ ሕዝብ የራቁ ቢሆንም አሁን ደግሞ የበለጠ የተገለሉበት መሆኑንም የደረሰን



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ዘገባ ጨምሮ ገልፆ ገና በትግል ላይ እያሉ የኢትዮጵያን ባንዲራ የዱቄት እና የስኩዋር መቋጠሪናያና ማሰሪያ አድርገውት አራት ኪሎ ቤተመንግስት ሲገቡ ደግሞ የሕወሓት ቁንጮ ጨርቅ እያለ የተከበረና ለአፍሪካ ነፃነት ተምሳሌት የሆነችውን ሀገር ባንዲራ ክፍ ዝቅ እያደረገ ለማዋረድ ሲጥር የነበረ መሆኑ አልበቃ ብሏቸው ዛሬ ደግሞ አህያን አልብሰው ማሳየታቸው ሕዝቡን እጅግ ያበገነና ያበሳጨ መሆኑን ካገኘነው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በረሀ አብራን ታግላለች ተብሎ ከታሰበ አህያዋን ማልበስ ያለባቸው የሕወሓትን ባንዲራ መሆን ሲገባው የነሱን ጨርቅ ክብር ጠብቀው የእምዬን ባንዲራ በእንዲህ ባለ ሁኔታ ማሳየታቸው አሳዛኝ፣ እና አንገብጋቢ እንዲሁም የሚያቃጥል የሀገሪቷን ሕዝቦች ምን ታመጣላችሁ በማለት የንቀት እርምጃ የወሰዱ መሆኑን በግልፅ ያሳዩበት ነው ሲሉ አንድ የቀድሞ የአባት ጡረተኛ እያለቀሱ ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

ወያኔ ይህን የመሰለ ታሪክ ይቅር የማይለው ርካሽ ተግባር ሲፈፅም መታየቱ በጣም አሳፋሪና አሳዛኝ ማንነታችንን የናደ መሆኑንም ሁኔታውን የተከታተሉ የሀገሪቷ ሕዝቦች እንባቸውን እያፈሰሱ በብስጭትና በንዴት ሲገልፁ መደመጡንም ዘገባው አብራቷል፡፡

ወያኔ በተለይም የሕወሓት ሹማምንቶች እርስ በእርሳቸውና በቀጠሯቸው ፖሊሶች ሳይተማመኑ በመቅረታቸው የተነሳ ከፌዴራል ፖሊስ ውስጥ የትግራይ ተወላጆች ብቻ ተመርጠው እንደተወሰዱና ለጥበቃ እነሱ ብቻ እንደተመደቡ ከሽሬ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀው ሻዕቢያም ሊደበደብ ይችላል በሚል ስጋት ቅዳሜ የካቲት 8 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ የሽሬ ከተማ ዙሪያ ያሉትን ኮረብታ ከፍታ ቦታዎች በከባድ መሣሪያና በወታደሮች ጥበቃ ማድረግ መጀመሩንም ገልፀዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ በኑሮ ውድነት እየተጠበሰ ባለበት በዚህ አስቸጋሪ ወቅት የወያኔ ባለሥልጣናት ለሕዝቡ ሲኦል የሆነበትን 33ኛ ዓመት ለማክበር በሚል ከ100 ሺህ ብር በላይ ወጪ ተደርጎ የርችት ተኩስ የተካሄደ ሲሆን ሌሎችም ዝግጅቶች ከሀገሪቷ ገንዘብ ወጪ ተደርገው የተከናወነ መሆኑ ታውቋል፡፡

በሽሬ እንደስላሴ የሕወሓት 33ኛ ዓመትን ለማክበር በተዘጋጁበት በዋዜማው የካቲት 10 ቀን 2000 ዓ.ም በ10 ማሊዮን ብር ከ25 ኪሎ ሜትር በላይ የቧንቧ መስመር ተዘርግቶ የውሃ ተጠቃሚ ማድረጋቸውንም በዚሁ ወቅት የተገለፀ ሲሆን እዚሁ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

መሀል ሀገር ጉድጓድ ቆፍሮ ውሃ ለማውጣት በጀት አልተያዘም እየተባለ በጀቱ ወደዚያው እየዞረ መሆኑን የገለፁት አንድ የግምጃ ቤት ሠራተኛ ይህም በጣም ትንሽ ነው ከሌሎች ክልሎች እየተቀነሰ ለትግራይ የሚሰጠውን በደንብ ብትመለከቱ የሚገርም ነው ሲሉ ገልፀዋል::

አክለውም የሚሰጠው ገንዘብ ለሕዝቡ የሚውል ቢሆን በጣም ጥሩ ነው:: ሕዝባችን ወገናችን ስለሆነ አይከፋንም:: ነገር ግን በሕዝቡ ስም እየወጣ የሕወሓት ባለሥልጣናት በረሀ የደከምንበት በመሆኑ ድርሻችን ነው እየተባባሉ ከትንሹ እስከ ትልቁ ሹማምንት እየተራኮቱ ይቃራመቱታል ሲሉም ገልፀዋል::

በትግራይ ከ40 በላይ ከፍተኛና በምስራቅ አፍሪካ ተወዳዳሪ ያልተገኘላቸው ፋብሪካዎች ተተክለው እየሰሩ ቢሆንም ለሕወሓት ባለሥልጣናት ኪስ ማደለቢያ ካልሆነ በስተቀር ለሕዝቡ አንዳችም ፋይዳ ያልሰጡ መሆኑን የገለፁት እኚሁ የግምጃ ቤት ሰራተኛ አሁንም በሕዝቡ መነገዳቸውን አላቆሙም ካሉ በኋላ በአሁኑ ሰዓት የአቶ መለስ ባለቤት ወ/ሮ አዜብ መስፍን ከጐተራ እስከ ሀና ማሪያም የሚሰራውን ቀለበት መንገድ ኮንትራት ወስዶ የሚሰራው የግዙፍ ኮንስትራክሽን ድርጅት ባለቤት መሆኗ ለዚህ ለህዝብ ገንዘብ ዝርፊያ ምሳሌ መጠቀስ የሚችል ነው ሲሉ እኚሁ ባለሙያ ገልፀዋል::

የአዲስ አበባ ፖሊስን በግምገማ ወጥረዋቸው እንደሚገኙ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ዘገባ ገለፀ:: አምና የአዲስ አበባ ፖሊሶች እርስ በእርሳቸው እንዲናቆሩና በመሀላቸው ክፍተት ሲመጣ አንዱ የአንዱን ምስጢር ያጋልጣል በሚል የሕወሓት ባለሥልጣናት የተጠቀሙበት ስልት የተናደባቸው ወያኔዎች ዘንድሮም በተመሳሳይ ጠንካራ ግምገማ በአዲስ አበባ ፖሊሶች ላይ እያደረጉባቸው ሲሆን ከግምገማው እስከአሁን አንድም ነገር ያላገኙባቸው በመሆኑ ገምጋሚዎቹ በንዴት እየተከኑ መሆኑ ምንጮቹ ገልፀዋል::

የእርስ በእርስ ግምገማ ውጤት አላመጣ ያላቸው ወያኔዎች አሁን ደግሞ አዲስ ስልት አዘጋጅተው በዚያ ዙሪያ እንደ አዲስ መገምገም መጀመራቸውንም እነዚሁ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል::

በዚህም መሠረት ይላሉ ምንጮቹ በዚህም መሠረት «የትግራይ ተወላጅ ፖሊሶችን ትንቃላችሁ፣ የኢህአዴግ ታማኝ አይደላችሁም፣ ስራችሁን በአግባቡ አትሰሩም፣



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ጥፋተኛ ተብሎ የመጣውን በዋስ ትለቃላችሁ» በሚሉና በሌሎችም ምክንያቶች እየተለጠፈባቸው ቢያገመግሟቸውም ሁሉም የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ፖሊሶች አባል አቋም ወጥ መሆኑን በመረዳታቸው የድንጋጤ መንፈስ ውስጣቸው መፈጠሩን ምንጮቹ አስረድተዋል::

በሌላ በኩል ለወያኔ ቡድን እድሜ መቀጠል ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረገ ያለው ብአዴን አባል የሆነችው ምክትል አፈ ጉባኤ ወ/ሮ ሽታዬ ምናለ ጥር 28ቀን 2000 ዓ.ም በድንገተኛ ሕመም ጦር ኃይሎች ገብታ እንደነበር ተገለፀ::

የወያኔ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ የሆነችው ወ/ሮ ሽታዬ ምናለ የተባለችው የወያኔ ተላላኪና ጉዳይ አስፈፃሚ ጥር 28 ቀን ከሰዓት በኋላ እቤቷ ውስጥ እንዳለች ድንገት በመታማሟ የደነገጡት ቤተሰቦቿ ወደ ጦር ኃይሎች ሆስፒታል የወሰዷት ሲሆን፣ እዚያም እንደደረሰች ተረኛው ዶክተር የአንጀት መታጠፍ (አፔንዲክስ) መሆኑን በመግለፅ ወዲያውኑ ቀዶ ሕክምና ያደረጉላት ቢሆንም በወቅቱ የቀዶ ህክምና ሲደረግላት የመድከም ምልክት በማሳየቷ ትሞታለች ብለው ቤተሰቦቿ በመጯጯሃቸው ብቻ ቀዶ ህክምና ያደረጉላትን ዶክተር ወደ እስር ቤት ከትተዋቸው እንደነበረም ለቤተሰቦቿ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል::

እነዚህ ወገኖች እንደሚሉት ከሆነ ይሁን እንጂ ችግሩ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ በሕክምህና ባለሙያዎች እርብርብ ሴትየዋ ታክማ ወደ ቤቷ የተመለሰች ሲሆን፣ ዶክተሩም ዋስ ጥርቶ ከእስር ሊለቀቅ እንደቻሉ አስረድተዋል::

በየቀኑ በተለያዩ ሆስፒታሎች በአንዳንድ ምግባረ ብልሹ ባለሙያዎች ስህተት ምክንያት በርካታ ንፁሀን ዜጐች እየሞቱ አንድም ጠያቂ ያላገኙ ሲሆን የወያኔ ባለስልጣን ስለሆነች ብቻ የቀዶ ህክምና ያደረጉላትን የህክምና ባለሙያ በስልጣኗ ያለምንም ጥፋት ለእስር መዳረጓ የወያኔ ባለስልጣናት አይነተኛ መገለጫ ነው ሲሉ ጉዳዩን ሲከታተሉ የነበሩ ለቤተሰቦቿ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል::

በሌላ በኩል በአሁን ሰዓት የኑሮ ውድነቱ ከቀን ወደ ቀን እያሻቀበ በሚገኝበት ወቅት የተቸገር ሕዝብ ያገኘውን ይበላል በሚል እሳቤ የቃሊቲ ምግብ ድርጅት የተበላሹ ምግቦችን በጨረታ ለመሸጥ መዘጋጀቱ ታውቋል::



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የካቲት 3 ቀን 2000 ዓ.ም በወጣው በዚሁ የጨረታ ሰነድ ላይ እንደተገለፀው የተበላሹ ምግቦች መሆናቸው በግልፅ ተጠቅሶ ለሽያጭ እንደሚቀርቡ የተገለፁ ሲሆን፣ የተበላሹ ምግቦች መቃጠል ወይም ጉድጓድ ውስጥ መቀበር ሲገባቸው ለሕዝቡ ደንታ የሌለው ወያኔ በግልፅ በተበላሹ ምግቦች ህዝቡን ለመጨረስ ማሰቡን የሚያረጋግጥ መሆኑን የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ገልፀዋል።

ወያኔ ገንዘብ ለመሰብሰብ እንጂ ለሕዝቡ ደንታ የሌለው ቡድን መሆኑ ቀድሞም የታወቀ ሲሆን አሁን ግን አይን ያወጣና ጭራሽ ማን አለብኝነቱ እየጨመረ መጥቶ የተበላሹ ምርቶችን በጨረታ ለመሸጥ ማቅረቡ ፍፁም የለየለት አረመኔነቱን ያረጋገጠ ነው ሲሉ እነኚሁ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በንዴት ገልፀዋል።

ይኸው ለገንዘብ እንጂ ለሕዝብ ፍፁም የማይጨነቀው የወያኔ ቡድን በቅርቡ ተግባራዊ የሚሆን አዲስ ስልት ነድፎ መንቀሳቀስ መጀመሩን ከደህንነት ቢሮ ምንጮቻችን የተገኘው ዘገባ አጋለጠ።

ለብዙ ጊዜ በደብቅ የወያኔ ባለስልጣናት ሲመክሩበት ሰንብተው በቅርቡ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘጋጁበት ደብረዘይት ከተማን በፌዴራል ቁጥጥር ስር ለማድረግ መሆኑን የምንጮቹ ጥቆማ አጋልጦ ይህ የሆነበት ደግሞ ከአዲስ አበባ እስከ ደብረዘይት ድረስ በሙሉ የኢንዱስትሪ መንደር በመሆኑና ይህንንም አመታዊ ግብር ለመሰብሰብ ታቅዶ መሆኑንም ሳይሸሽጉ ገልፀዋል።

በዓመት በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ግብር የሚያስገቡት እነዚህ ፋብሪካዎች በአሁን ሰዓት ተጠሪነታቸው ለኦሮሚያ ክልል ሲሆን፣ አሁን ባለው እቅድ ተግባራዊ ከሆነ ግን ለፌዴራል ሀገር ውስጥ መሆኑን ገልፀዋል።

ሌላው የምንጮቹ ጥቆማ ከአዲስ አበባ እስከ ደብረዘይት ድረስ ያሉት ፋብሪካዎች ከግማሽ በላይ የትግራይ ተወላጆች ንብረት በመሆኑ ለሕልውናችን አስተማማኝ ሁኔታ የሌለ በመሆኑ ዋስትናችን ምንድነው? በማለት ለወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በተደጋጋሚ ጊዜ አቤቱታ እንዳቀረቡ አትቶ በዚህም ምክንያት የፌዴራል መንግስት ቁጥጥር ስር አስገብቶ ከኦሮሚያ ለመንጠቅ መዘጋጀታቸውንም ጨምረው ገልፀዋል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በአሁን ሰዓት ይህንን ጉዳይ የደብረዘይት ከተማ ነዋሪዎች በመስማታቸው የተነሳ ወጣቶቹ ተቃውሞ ሊያነሱ ይችላሉ ተብሎ ስጋት ስለተፈጠረ በመቶዎች የሚቆጠሩ የሀገር ውስጥ ደህንነት ሰራተኞች ወደ ደብረዘይት ገብተው የስለላ ተግባራቸውን እያከናወኑ መሆኑንም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል።

የደብረዘይት ከተማን በፌዴራል ስር ለማድረግ ሽር ጉድ እያሉ ባለበት ወቅት «የሱማልያ ክልል ከቁጥጥራችን ውጭ እየሆነ ስለሆነ አስቸኩዋይ እርምጃ እንዲወሰድና እልባት እንዲሰጠን» በሚል ከወያኔው መሪ ቢሮ አዲስ መመሪያ በመውጣቱ ሰሞኑን የደህንነትና የወታደራዊ አዛዦች በጅጅጋ ሽማግሌዎችን ሰብስበው ሲያስፈራሩ እንደሰነበቱ ከጅጅጋ ከተማ የደረሰን ዘገባ ገለፀ።

የወያኔ ከፍተኛ የደህንነት ባለሥልጣናትና የጦር አዛዦች በጋራ በመሆን የሱማሌ ክልል የሐገር ሽማግሌዎችን በግዳጅ በመሰብሰብ በኦጋዴን ክልል ለደረሰው የሰው ሕይወት መጥፋትና ለወደመው ንብረት ተጠያቂው የኦጋዴን ነፃ አውጪ ግንባር ነው ብላችሁ ፈርሙ በሚል ያስፈራሯቸው ቢሆንም «እኛ መፈረም አንችልም። እናንተ በእኛ ስም የፈለጋችሁትን ነገር መግለፅ ትችላላችሁ» በማለት ባለመስማማት የተለያዩ ሲሆን የወያኔ ቡድን ግን ግንባሩ የፈፀመው ነው በሚል በሀገር ሽማግሌዎቹ ስም መግለጫ ያወጣ ሲሆን፣ ይኸው ዘገባ በመገናኛ ብዙኃን በመተላለፉ የሐገር ሽማግሌዎቹ እንደተበሳጩ ከጅጅጋ የደረሰን ዘገባ አረጋግጧል።

በተለይም በጅጅጋ ከተማ በዘመዶቻቸው ቤት ውስጥ ተጠልለው ያሉት የኦጋዴን ነዋሪዎች ወያኔ በእግረኛ ለመቋቋም ሲያቅተው በጀትና ሔሊኮፕተር ድብደባ በመፈፀሙ በርካታ ዜጐች በቦምብ ፍንጣሪ እጃቸውን እና እግራቸውን የተቆረጡ መኖራቸው የታወቀ ሲሆን እነዚህን ጉዳተኞች በመሰብሰብ በገንዘብ በመደለልና በማስፈራራት ፊልም ለመስራት ቢያስብም እነሱ እምቢ ማለታቸውን ይኸው የደረሰን ዘገባ ገልፆ በደረሰባቸው የቦምብ ድብደባ አካላቸውን ማጉደሉ ሳያንሰው ለሀሰተኛ ፊልም ስራ ተባበሩኝ በማለት የቁም ስቅል እያሳያቸው እንደሚገኝም የደረሰን ዘገባ አጋልጧል።

በዚሁ ክልል ከኦብነግ ጋር ግንኙነት አላቸው በሚል ቁጥራቸው ከ450 በላይ የክልሉ ተወላጅ የፖሊስ መኮንኖች ከስራ ካባረረ በኋላ ከመሀከላቸው የተማሩ ናቸው የተባሉትን እየመረጠ ወደ ዘብጥያ እንዳስገባቸውም ይኸው ዘገባ አጋልጧል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የወያኔ ባለስልጣናት የሕወሓት ምስረታ በዓልን ምክንያት በማድረግ በትግራይ በደስታ እያከበሩ ባለበት ወቅት መላው የሀገሪቱ ሕዝብ በችግርና በችጋር እየተጠበሰ ሲሆን፣ የሱማሌ ክልል ተወላጆች ግን ከረሀቡ በተጨማሪ የወያኔ ተኩላ ደህነቶችና የጦር አዛዦች ከፍተኛ ግፍ እየተፈፀመባቸው እንደሚገኝም ይኸው ከጅጅጋ የደረሰን ዘገባ አጋልጧል፡፡



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com